# Hazards on your property after a bushfire

# ከጫካ እሳት በኋላ በንብረትዎ ላይ አደጋ ላይ መጣል

Amharic

## መግቢያ

በጫካ እሳት የተቃጠሉ ቤቶች፣ መጠለያዎችና ሌሎች ህንጻዎች ወይም አካል ላይ በቀሩት ስብርባሪዎችና አመድ በጤና ላይ አደጋ ሊፈጥሩ ይችላሉ። በቤት ውስጥ ያሉ ቆሳቁሶች አደገኛ ከእሳቱ በኋላ ማለት አስቤስቶስ፣ ከጣውላ ቃጠሎ የተፈጠረ አመድ (ይህም copper chrome arsenate or ‘CCA’)፣ መድሃኒቶች፣ የጓሮ አትክልት ወይም የ እርሻ ኬሚካሎች፣ ሌላ አጠቃላይ ኬሚካሎች (ለምሳለ፡ የጽዳት ውጤቶች፣ የገንዳ ክሮኒክ ወዘተ.)፣ ከቤት እቃዎችና መገልገያዎች ቃጠሎ የብረትና ሌላ ቅሬቶች እንዲሁም አመድና ብናኞች ይሆናሉ።

ንብረትዎን ለማየት ከመሄድዎ በፊት (የተረፈውን ግላዊ እቃዎች ወይም ለማጽዳት ቅንጅት ለማድረግ) የርስዎን ጤንነት ለመከላከል ሲባል የሚከተሉትን ነገሮች ግምት ውስጥ ማስገባት ይሆናል። ለደህንነት ሲባል ጎልማሶች እንዳይሄዱ ማቀብ ነው።

## በቦታው ላይ ከመሄድ በፊት

- የኤሌትሪክ አደጋ ሊኖር ይችላል ማለት እንደ የወደቀ “ያልጠፋ” የሃይል ገመድ መስመር ሊኖር ይችላል። ወደ ንብረቱ ለመግባት የማያሰጋ መሆኑ እስኪነገርዎ ድረስ አይግቡ (ይህም ከድንገተኛ አገልግሎት፣ ከመገልገያ ወይም ከአካባቢ ምክር ቤት ባለስልጣኖች)።
- በህንጻዎችና ሌሎች የህንጻ አካላት ላይ መግባቱ ወይም በዚያ በእግር መራመዱ ጥሩ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ የተበላሹትን እቃዎች ከመጠገን ወይም የሆነ የማጽዳት ሥራ ከመፈተንዎ በፊት ለመግባት ደህንነቱ የማያሰጋ ስለመሆኑ ምክር ከርስዎ ምክር ቤት የህንጻ ክፍል ማግኘት ነው።
- ትኩስ፣ የሚጤስ ክሰልና ሌሎች አደጋ ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮች በስብርባሪው ስር የተደበቀ ሊኖር ስለሚችል ነው። ለምሳሌ፣ በርስዎ ህንጻ ላይ የአስቤስቶስ ስሚንቶ ቁርጥራጭ የያዘ ሊሆን ስለሚችል ታዲያ የህንጻን ስብርባሪ በሚያስተካክሉበት ጊዜ ተጨማሪ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል።

## በአለባበስ ስለመከላከል

- ከተሰባበረ መስተዋት፣ ከስለታማ ላይ ሲቆሙ ወይንም ከድንጋይ ከሰል ረመጥ ቃጠሎ እራስዎን ለመከላከል ጠንካራ ጫማ ማድረግና በጣም ጠንካራ የሆነ ጓንት ማጥለቅ ይሆናል።
- ሙሉ ሰውነትን ተከላካይ የሆነ ቱታ (ረጅም እጀታዎችና ሱሪዎች ጋር) ማድረግ። አመቺ ከሆነ ለአንድ ጊዜ የሚጠቅም መሸፈኛ መጠቀምና ከተጠቀሙ በኋላ በቦታው ከሚሰበሰቡት ቆሻሻዎች ጋር መጣል ይሆናል። ማንኛውም የዚህ አይነት የሸፋን ልብሶች እንደገና ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት (ጫማንም ያካተተ) መጣጠብ አለባቸው።

## የፊት ጥንብል ስለማድረግስ ምን ይመስላል?

- ማንኛውም የወረቀት ብናኝ ጭምብል፣ መሃረም ወይም የአንገት ልብስ ከአደጋው በኋላ የቀሩትን ጥቃቅን የሆነ አመድ ወይም ብናኝ ወይንም የአስበስቶስ ንጥረ ነገር እንደማያጠአራ ነው። ስለዚህ እነዚህ በአጠቃላይ የርስዎን ሳንባ ለመከላከል በጣም ጠቃሚ አይደሉም።
- የአስበስቶስን ንጥረ ነገር ያቀፈ ለማጣራት ልዩ የሆነ ጭንብል (‘P1’ or ‘P2’ ይባላል) ማድረግ ያስፈልጋል። በአብዛኛው የህንጻ መሳሪያ መደብሮች ይገኛሉ። ‘P2’ የጭምብል ከ‘P1’ በበለጠ ጥቃቅን የሆኑትን ነገሮች ያጣራል።
- በሚገባ ለመተንፈስ ለርስዎ የፊት ጭምብል ማጥለቁ ከባድ ሊሆን ይችላል። ቀደም ሲ የልብ ወይንም የሳንባ ችግር ካለብዎ ከመጠቀምዎ በፊት ከሐኪምዎ ምክር ያስፈልግዎታል።
- በአፍና በአፍንጫ ዙሪያ በደንብ ካልታሸገ የዚህ አይነቱ ጭምብል አነስተኛ ጥቅም እንዳለው ማወቁ ጠቃሚ ይሆናል። ጢም ያላቸው ወንዶች ጥሩ ሽፋን ያለውን ለማግኘት ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል።

## ቅሻሻን ስለመቆጣጠር

- የህንጻ ሽክላ/ድንጋይ ስብርባሪ ቦታው ላይ ወይም በአጠገብ ባለ ቦይ መቀበር አለበት፣ ምክንያቱም በቆሻሻው ውስጥ አደገኛ የሆኑ መርዛም ነገሮች ስለሚኖሩ ለአካባቢው መሬትና ማህበረሰብ ጉዳት ሊፈጥሩ ይችላሉ።
- በተለይ አመዱን በንብረትዎ ላይ አይበትኑት፣ ይህም በቤትዎ ወይም ሌላ ህንጻ አካል ላይ አስበስቲስ ከነበረ፣ ወይም በCCA ኬሚካል የተቀባ ጣውላ ካለና ከተቃጠል ይሆናል።
- ማንኛውንም ጥራጊ፣ አመድ ወይም ሌላ ቆሻሻ ከመቆጣጠርዎ በፊት የመከላከያ ልብስ/መሣሪያ ማድረግ አለብዎ።
- ያመዱን ብናኝ ለመቀነስ በውሃ ማርጠብ ነው። ለዚህ ጉዳይ ከፍተኛ ግፊት ያለው የውሃ መርጫ ብናኙን/ አመዱን ሊበትን ስለሚችል አለመጠቀም ነው።

## የአስበስቶስ አደጋዎች — ማጽዳትና መጣል

- ከ1988 ዓ.ም በፊት በህንጻ ግድግዳ፣ በጣራ፣ በወለል በታች፣ በጣራ ከፈፍ፣ በአንዳንድ የጢስ ማውጫ የወለል ለበስ ላይ አስበስቶስ ስሚንቶ (ወይም 'AC') ሊኖረው ይችላል። እነዚህ ቁርጥራጭ ነገሮች በአጠቃላይ ለጤና አስጊ አይደሉም ይሁን እንጂ እነዚህን ለማምረት ሲጀመር ሲቆረጥ፣ ሲሰባበር ወይም ሲያይዙት ካልሆነ በስተቀር።
- በጫካ እሳት ጊዜ ወደ አየር የሚሄደው የአስበስቶስ ንጥረ ነገር መጠን አነስተኛ ይሆናል።
- ከጫካ እሳት በኋላ በሚጸዳበት ጊዜ ወይንም ህንጻ በሚፈርስበት ጊዜ አስበስቶሱ ስለሚነካካ ጥቃቅን ብናኙ አየሩን ይበክላል። በንብረትዎ ላይ አስበስቶስ ካለበት ታዲያ ፈቃድ ያለው የአስበስቶስ አስወጋጆች በማጽዳቱ ሥራ ላይ መቀጠር አለባቸው። ቆሻሻው በEP ተቀባይነት ባገኘ መጓጓዣ ተሽከርካር መሆን እንዳለበትና ይህም በተፈቀበት EPA መሬት ማስተካከያ መጣል አለበት።
- በቆሻሻ ማስወገጃ ሥራ ጊዜ የሚገኙ ከሆነ የ'P2' ፊት ጭምብል ማጥለቅ አለብዎ።
- በርስዎ ቦታ ላይ ያለው አስበስቶስ የያዙ ነገሮች ካልተቃጠሉና ጥቂት የAC ቁራጮች ከሆኑ በወፍራም ፕላስቲክ ከረጢት (ወይም ለትንሽ ቁራጭ የሚሆን ድርብ ፕላስቲክ ከረጢቶች) ውስጥ ማስገባትና በምክር ቤት ወይም በቪክቶሪያ EPA መሬት ማስተካከያ ፍቃድ ባለው ቦታ ላይ ወስዶ መጣል።

## Ash from burnt በCCA- ከተቀባ ጣውላ የቃጠሎ አመድ — ማጽዳትና ማስወገድ

- "CCA" ይህ ማለት copper chrome arsenate ሲሆን ብዙጊዜ ጣውላዎችን ከተባይ ለመከላከል የሚቀባ ኬሚካል ይሆናል። በ CCA ኬሚካይ የተቀባ ጣውላ የሚያገለግለው ለበረንዳ፣ ለመርከብ መድረክ ወለል፣ ለጎጆ ቤት፣ ለመሸፈኛ፣ ለማእዘን ቋሚ እንጨት፣ ለበር፣ ለአጥርና ለመሬት ማስተካከያ መሥሪያ ይሆናል። ከእሳት ቃጠሎ በኋላ የሚቀረው አመድ ከመቶ 10% arsenic, copper and chromium (በክብደቱ) የሚሆን ኬሚካሎች ይይዛል።
- ህጻናት በበለጠ ነገሮችን ወደ አፋቸው ማስገባት ይችላሉ። የበሉት መጠነኛ ግራም ብቻ ቢሆንም አደገኛ እንደሆነ ነው። እንዲሁም እንስሳት ጨዋማ የሆነን አመድ በመላስ ወይም በመብላት ሊመረዙ ይችላሉ። ስለዚህ እነዚህ አምድ ያለበት ቦታዎች እስኪጸዱ ድረስ ህጻናት፣ የቤት እንስሳትና ሌሎቹም መራቅ አለባቸው።
- አመዱ በድርብ ከረጢት ታሽጎ በቀጥታ ወደ አካባቢ የመሬታ ማስተካከያ ሙሌት ላይ መጣል ይኖርበታል። እንዲሁም የተሰባበረ ጣውላም በዚሁ ላይ መጣል ይቻላል። በCCA ኬሚካል የተቀቡ ጣውላዎች የሚከሰት አካባቢያዊ ችግር መፍጠር በተመለከተ ስለአካባቢ ለሚያስፈልጉ በበለጠ ምክር ለማግኘት EPA ማነጋገር።

## ለበለጠ መረጃ

በጫካ እሳት ጢስ መጋለጥ ስለሚከሰት የጤና ምክር ወይም ከጫካ እሳት በኋላ ስለሚቀሩ ነገሮች በተመለከተ ሐኪምዎን ማነጋገር።

ስለ አሰበስቶስ አጠቃላይ የጤና መረጃ ለማግኘት  የCCA ወይም

ስለሌላ ኬሚካል በተመለከተ በሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የአካባቢ ጤና ክፍልን (DHS) በልክ 1300 761 874 ማነጋገር ነው።

ስለ የአደገኛ ነገሮችን (ለምሳሌ አስበስቶስ) ማጓጓዣና መጣያ ቦታ መረጃ ለማግኘት  ለቪክቶሪያ EPA በስልክ (03) 9695 2722 ወይም 1800 444 004 (በነጻ) ደውሎ ማነጋገር ነው።

ስለ ህንጻ ፍርስራሽ፣ አመድን እንደ ሠራተኛ ሆኖ ለመቆጣጠር በተመለከተ መረጃ ለማግኘት በቪክቶሮያ የሥራ ደህንነት/ WorkSafe Victoria በስልክ (03) 9641 1555 ወይም 1800 136 089 (በነጻ) ደውሎ ማነጋገር ነው።

ስለጫካ እሳትና የህዝብን ጤንነት በተዛመደ በሌሎች ወረቀቶች ይካተታል: የጫካ እሳት ጢስና የርስዎ ጤንነት፣ እንዲሁም በጫካ እሳት በተበከሉ ቦታ ላይ ከውሃ ማጠራቀሚያ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ምክር። ሁለቱም ከዌብሳይት www.health.vic.gov.au/environment/emergency_mgmnt/index.htm#bushfires ማግኘት ሲቻል ወይም በሰብ አዊ አገልግሎት መምሪያ የአካባቢያዊ ጤና ጥበቃ ክፍል በስልክ 1300 761 874 በመደወል ማግኘት ይቻላል።

በሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የአካባቢና ጤና ጥበቃ ክፍል በኩል የታተመ ቀን: ጥቅምት/ October 2006 ዓ.ም

State Government Victoria Department of Human Services